

DEBRE TSION SAINT MARY EHTIOPIAN ORHTODOX TEWAHEDO CHURCH
PORTLAND OREGON
ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፖርትላንድ ኦሪገን

www.debretsioneotc.org

# Mezmur /መንፈሳዊ መዝሙር

(1) Aman beaman
(2) Andebtim yawuta yemisgana kina
(3) Gebriel new alu
(4) Kibre kidusan yeiti
(5) Medahinialem adenen
(6) Menfes kidus worede
(7) Nesebiho (2) leigzihabher
(8) O Michael (2) like melaikit
(9) Selam leki
(10) Yefikir enat yeselam
(11) Kegetaye fikr yemilegn
(12) Elil belu beandinet zemiru
(13) Moged simetagn maibelu
(14) Silemayneger sitotaw egziabher yimesgen
(15) Yeawaj negari kal bebereha ale
(16) Awude amet lebarko
(17) Yemeskel Mezmur
(18) Hail yeiziabher new
(19) Zemene Tsige
(20) Tsilat zemuse etsepatos zesina
(21) Kidane Mihiret emebet
(22) Egziabher birhanena medhanita
(23) Emebeta Mariam eleminish
(24) Michale slew smun stera
(25) Yeyard wub zema dingil
(26) Yalante lena man lihonegn
(27) Enameseginh alen
(28) Zemir zemir alegn liba

**Menfes kidus worede** laile hawariyat (2)
Temesilo temesilo (2) temsilo benede esat

**Nesebiho (2) leigzihabher (2)**
Sibuha zetesebiha (2)
Enamesginew (2) egiziabherin
Misgun new yetemesegen (2)

**Medahinialem adenen bemayshar kalu (2)**
Des yibelen (2) elil belu (2)
Adanen bemayshar kealu

**መንፈስ ቅዱስ ወረደ** ላእለ ሐዋርያት (2)
ተመሲሎ ተመሲሎ (2) ተመሲሎ በነደ እሳት

**ንሴብሖ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር (2)**
ስቡሐ ዘተሰብሐ (2)
እናመስግነው እናመስግነው (2) እግዚአብሔርን
ምስጉን ነው የተመሰገነ (2)

**መድኃኔዓለም አዳነን** በማይሻር ቃሉ (2)
ደስ ይበለን (2) እልል በሉ (2)
አዳነን በማይሻር ቃሉ፤

## Yefikir enat yeselam (2)

Yinafikegnal simish salteraw siker Mariam

Behiwote wust benuroye
Kidemi kefit kehualaye
Tedeladele libe
Anchi aleshina kategebe

Azmach---------

Mignotem yismer tilk hilme
Lilef wjebun tekuakume
Yegetaye enat nesh
Hailin yadergal tselotish

Azmach-----------

## የፍቅር እናት

የፍቅር እናት የሰላም (2)

ይናፍቀኛል ስምሽ ሳልጠራው ስቀር ማርያም

በሕይዎቴ ውስጥ በኑሮዬ
ቅደሚ ከፊት ከኋላዬ
ተደላደለ ልቤ አንቺ አለሽና ከአጠገቤ

አዝማች-------------

ምኞቴም ይስመር ትልቅ ሕልሜ
ለለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ
የጌታ እናት ነሽ ኃይልን ያደርጋል ጸሎትሽ

አዝማች-----------

Endate ekeralehu kemengede

Adera enate asibign

Kemiaschenikegn telat

Lmiyasadidegn atischign

Azmach----------

Tinantim zarem amesgagn negn

Yelem lenege yemiasferagn

Meda yihonal terara

Lijish silale kena gara

Azmach----------

እንዴት እቀራለሁ ከመንገድ

አደራ እናቴ አስቢኝ

ከሚስጨንቀኝ ጣላት ለሚያሳድደኝ አትስጭኝ

አዝማች----------

ትላንትም ዛሬም አመስጋኝ ነኝ

የለም ለነገ የሚያስፈራኝ

ሜዳ ይሆናል ተራራ ልብሽ ስላለ ከኔ ጋራ

## Selam leki

Selam Selam leki Mariam selam leki /2/

Yehiwot meseret -- Selam leki

Yehiwot alegnita -- Selam leki

Dingil aderashin -- Selam leki

Hugnilin mekata -- Selam leki

Azmach----------

Bela seb dane -- Selam leki

Bizu nefis atifto -- Selam leki

Yeanchin sim letera -- Selam leki

Tirign wuha seto -- Selam leki

Azmach---------

## ሰላም ለኪ

ሰላም ሰላም ለኪ ማርያም ሰላም ለኪ /2/

የሕይወት መሠረት......ሰላም ለኪ

የፍጥረት አለኝ ...... ሰላም ለኪ

ድንግል አደራሽን ...... ሰላም ለኪ

ሁኚልን መከታ ...... ሰላም ለኪ

አዝማች -----------

በላዔ ሰብእ ዳነ ...... ሰላም ለኪ

ብዙ ነፍስ አጥፍቶ ...... ሰላም ለኪ

የአንቺን ስም ለጠራ ...... ሰላም ለኪ

ጥርኝ ውኃ ሰጥቶ ...... ሰላም ለኪ

አዝማች --------------

Tematsinenibishal -- Selam leki
Beamalajinetish -- Selam leki
Dingil aderashin -- Selam leki
Amaljin kelijish -- Selam leki
Azimach-------------

Egnam biiketal -- Selam leki
Bego migbarin -- Selam leki
Behiwot beselam -- Selam leki
Eninoralen -- Selam leki
Azmach-------------

Yelibonachew ber -- Selam leki
Letezegabachew -- Selam leki
Endiameseginush -- Selam leki
Dingil hoy erjachew -- Selam leki
Azmach-------------

ተማጽነንብሻል ...... ሰላም ለኪ
በአማላጅነትሽ ...... ሰላም ለኪ
ድንግል ሆይ አደራ ...... ሰላም ለኪ
አማልጅን ከልጅሽ ...... ሰላም ለኪ
አዝማች -------------

እኛም ብንከተል ...... ሰላም ለኪ
በጎ ምግባርን ...... ሰላም ለኪ
በሰላም በጤና ...... ሰላም ለኪ
እንኖራለን ...... ሰላም ለኪ
አዝማች -------------

የልቦናቸው በር ...... ሰላም ለኪ
ለተዘጋባቸው ...... ሰላም ለኪ
እንዲያመሰግኑሽ ...... ሰላም ለኪ
ድንግል ሆይ እርጃቸው ...... ሰላም ለኪ
አዝማች--------------

## O Michael (2) like melaikit

Behatiat endanwodk endanimot

Fetineh teradan antsinan beimnet

Azmach------------------

Leyakob neged --- Michael

Leisrael --- Michael

Tebakiachew neh --- Michael

Meliake hail --- Michael

Fikrin adilen mihiret

Kidus michael yegna abat /2/

Azmach-------------

Netsebrakawi --- Michael

Tekhino libsih --- Michael

Hamelmale worke --- Michael

Aynu zerigb --- Michael

Fikrin adilen mihiret

Kidus michael yegna abat /2/

## አ ሚካኤል

አ ሚካኤል /2/ ሊቀ መላእክት
በኃጢያት እንዳንወድቅ እንዳንሞት
ፈጥነህ ተራዳን አጽናን በእምነት
አዝማች---------------

ለያዕቆብ ነገድ ለእሥራኤል
ጠባቂያቸው ነህ መልአከ ኃይል
ፍቅርን አድለን ምሕረት
ቅዱስ ሚካኤል የእኛ አባት/2/
አዝማች-----------------

ነፀብራቃዊ ተክህኖ ልብስህ
ሐመልማለ ወርቅ ዐይኑ ዘርግብ
ፍቅርን አድለን ምሕረት
ቅዱስ ሚካኤል የእኛ አባት /2/

Besilih fit --- Michael

Esegidalehugn --- Michael

Fetineh aregagagn --- Michael

Alehu belegn --- Michael

Fikrin adilen mihiret

Kidus michael yegna abat /2/

Azmach---------------

በስዕልህ ፊት እሰግዳለሁኝ
ፈጥነህ አረጋጋኝ አለሁ በለኝ
ፍቅርን አድለን ምሕረት
ቅዱስ ሚካኤል የእኛ አባት/2/

አዝማች-----------------

| | |
|---|---|
| **Aman beaman (2)** | **አማን በአማን (2)** |
| Mengiste silassie zelealem (2) | መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም (2) |
| **Gebriel new** alu asdesach melak (2) | **ገብርኤል ነው አሉ** አስደሳች መልአክ (2) |
| Tirguamewum sewna amlak  (2) | ትርጓሜውም ሰውና አምላክ (2) |
| Kirkos kenatu gar beisat sitalu (2) | ቂርቆስ ከእናቱ ጋር በእሳት ሲጣሉ (2) |
| Wuha hone tefa nebelbalu (2) | ውሃ ሆነ ጠፋ ነበልባሉ (2) |

**Kibre kidusan yeiti (2)**

Mudaye mena girum /2/…Azmach

Yekidusanu kibir neshina
Ensetish alen kina misgana
Yewoledshilin yehiwot mena
Zinab yalebish tanash demena
Azmach-------------

Titina libsish fikir wubetish
Tsins yazelilal selamita dimtsish
Esatun woldesh esat takifeshal
Sanzemirilish meche yimeshal
Azmach--------------

**ክብረ ቅዱሳን ይእቲ (2)**

ይእቲ ክብረ ቅዱሳን/2/
ሙዳየ መና ግሩም/6/ (አዝማች)

የቅዱሳኑ ክብር ነሽና
እንሰጥሻለን ቅኔ ምስጋና
የወለድሽልን የሕይወት መና
ዝናብ ያለብሽ ታናሽ ደመና
አዝማች------------

ትህትና ልብስሽ ፍቅር ውበትሽ
ጽንስ ያዘልላል ሰላምታ ድምጽሽ
እሳቱን ወልደሽ እሳት ታቅፈሻል
ሳንዘምርልሽ መቼ ይመሻል

Yetsehay mewucha misrak honesh

Talakun birhan ayenebish

Atichelimim hiwotachin

Lijish eskale tsehayachin

<u>Azmach</u>----------------

Seali len selam leki

Temahitsene bekidanki

Niai rigbiye misle woldki

Semay womidir yawodisuki

<u>Azmach</u>--------------

የፀሃይ መውጫ ምስራቅ ሆነሽ
ታላቁን ብርሃን አየንብሽ
አትጨልምም ሕይወታችን
ልጅሽ እስካለ ፀሃያችን

<u>አዝማች</u>--------------

ሰአሊለነ ሰላም ለኪ
ተማህፀነ በኪዳንኪ
ንኢ እርግብየ ምስለ ወልድኪ
ሰማይ ወምድር ያወድሱኪ
<u>አዝማች</u>----------------

## Andebtim yawuta yemisgana kina

Yeamilaken madan aychalehu bayna
Begebaon seamy tsehayin yakome
Zarem gobignitognal eyedegageme
Azmach-------------------

Wetimed tesebere enam ameletikugn
Ketelat filatsa kemot awotahegn
Yeanabistun af behailu yezega
Yedaniel amlak yinoral kena ga
Azmach-----------------

## አደበቴም ያውጣ የምስጋና ቅኔ

የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ ባይኔ
በገባኦን ሰማይ ፀሐይን ያቆመ
ዛሬም ጎብኝቶኛል እየደጋገመ
አዝማች-----------------

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከጠላት ፍላፃ ከሞት አወጣኸኝ

የአናብስቱን አፍ በሀይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከኛጋ
አዝማች-----------------

Bedawit misgana beyared zimara
Kekidusan gara lizemir abira

Esun samesegin melkol bitsikibign

Legetaye kibir ezemiralehugn

Azmach-------------

Asferiw nebelbal esatu binedim

Letaot alsegidim negestat biyawujum

Hulum bitewuchigm bitelagnim alem

Tsinat yihonegnal geta medehinealem

Azmach-------------

በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ
ከቅዱሳን ጋራ ልዘምር አብሬ
እሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብስቅብኝ
ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ
አዝማች---------------

አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነደድም
ለጣኦት አልሰግድም ነገስታት ቢያውጁም
ሁሉም ቢተወኝም ቢጠላኝም ዓለም
ፅናት ይሆነኛል ጌታ መዳኃኔዓለም
አዝማች---------------

**Kegetaye fikr** yemilegn man new (2)
Mekera chigir sikay wois merakot new (2)
Anferam ansegam aniteraterim (2)
Egiziabher kegna gara yinoral lezelealem (2)
Yesemay betachin amanuel yeseraw (2)
Ginbu nitsuh wuha meseretu dem new (2)
Saynega teramiden enguaz tewat (2)
Bedemu mesirto keseralin bet (2)
Yewuha gidgida yedem meseret (2)
Yihew kezih ale yeamanuel bet (2)

**ከጌታዬ ፍቅር** የሚለየኝ ማነው/2/
መከር ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው/2/
አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም/2/
እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም/2/
የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሰራው/2/
ግንቡ ንጹህ ውሃ መሰረቱ ደም ነው/2/
ሳይነጋ ተራምደን እንጓዝ በጠዋት/2/
በደሙ መስርቶ ከሰራልን ቤት/2/
የውሃ ግድግዳ የደም መሰረት/2/
ይኸው ከዚህ አለ የአማኑኤል ቤት/2/

**Elil belu** beandinet zemiru
Amesginu lekibru zemirulet
Ende egziabher yale manim yelem belu

Behatiat barinet sininor tegeziten
Kebetu sinirk tizazun afrisen
Ayto zim lalen telatochu salen
Wuletaw bizu new kibir lersu yihun (2)
Azmach

Rasun awardo egnan akeberen
Sigawuna demu bilu tetu alen
Melkam eregna new yemiasatan yelem
Misgana yidresew lemedahine alem (2)

**እልል በሉ** በአንድነት ዘምሩ
አመስግኑ ለክብሩ ዘምሩለት
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም በሉ
አ.ዝ................//

በኃጢያት ባርነት ስንኖር ተገዝተን
ከቤቱ ስንርቅ ትእዛዙን አፍርሰን
አይቶ ዝም ላላለን ጠላቶቹ ስንሆን
ውለታው ብዙ ነው ክብር ለዕርሱ ይሁን/2/

አ.ዝ ............//
ራሱን አዋርዶ እኛን አከበረን
ሥጋውና ደሙን ብሉ ጠጡ አለን
መልካም እረኛ ነው የሚያሳጣን የለም
ምስጋና ይድረሰው ለመድሐኔአለም/2/
አ.ዝ ..................//

Hiwotun yesewa ende amlak man ale
Lesew lijoch bilo bemeskel yewale
Fikru ayleka ayalkim biwora
Kesemayat wordo hone kegna gara (2)
Azmach

Sirawun enadink endih lewodeden
Kemayalkew fikru Bereket ladelen
Lemaynegerew leamlak sitota
Wdasen enakrib ketuat eskemata (2)

ሕይወቱን የሰዋ እንደ አምላክ ማን አለ
ለሰው ልች ብሎ በመስቀል የዋለ
ፍቅሩ አይለካ አያልቅም ቢወራ
ከሰማያት ወርዶ ሆነ ከእኛ ጋራ/2/
አዝ………………//

ሥራውን እናድንቅ እንዲህ ለወደደን
ከማያልቀው ፍቅሩ በረከት ላደለን
ለማይነገረው ለአምላክ ስጦታ
ውዳሴን እናቅርብ እንዘምር በእልልታ /2/

## Moged simetagn maibelu

Man yadinewal hulum silu

Beslema alefku betsetita

Hulu techilo beante geta (2)

………azimach………

Beantes kusil tefewoskugn

Geta befikirih temarekugn

Moten shirehew beante mot

Yihew akomkegn behiwot (2)

………azimach………

Deji sitena simatsenih

Meche chekene geta libih

Ende kerachu agonebesku

Mihiret tsegahin keijih lebesku (2)

## ሞገድ ሲመታኝ ማዕበሉ

ሞን ያድነዋል ሁሉም ሲሉ
በሰላም አለፍኩ በፀጥታ
ሁሉ ተችሎ በአንተ ጌታ(2)

………..አዝ……
በአንተስ ቁስል ተፈወስኩኝ
ጌታ በፍቅርህ ተማረኩኝ
ሞቴን ሽረኸው በአንተ ሞት
ይሄው አቆምከኝ በህይወት(2)

………..አዝ……
ደጅህ ስጠና ስማፀንህ
መቼ ጨከነ ጌታ ልብህ
እንደ ቀራጩ አጎነበስኩ
ምህረት ፀጋህን ከእጅህ ለበስኩ(2)

Zewotir elil bil bizemir

Silegebagn new yeante fikir

Geta miterawu simihin

Lewutehew new tariken (2)

………azimach………

Aynoche eyayum keante beker

Yemitiwoded yemitifeker

Zemed wogena honehegnal

Einen yemichil yet yigegnal (2)

………azimach………

ዘወትር እልል ብል ብዘምር
ስለገባኝ ነው ያንተ ፍቅር
ጌታ ምጠራው ስምህን
ለውጠኸው ነው ታሪኬን(2)

...........አዝ......
አይኖቼ አያዩም ከአንተ በቀር
የምትወደድ የምትፈቀር
ዘመዴ ወገኔ ሆነኸኛል
እኔን የሚችል የት ይገኛል(2)

## Silemayneger sitotaw egziabher yimesgen

Chel yalen amlak singwaz maibelun akuarten

Silemayneger sitotaw egiziabher yimesgen

………azimach………

Yehiwot estinfas zerabin hiyaw endinihon

Yihin laderege amilakachin egiziabher yimesgen

Silemayneger sitotaw egiziabher yimesgen

………azimach………

Nefasin gesitso maibel akumo yemiashagir

Yealme fetena bibeza esu metegiachin

Silemayneger sitotaw egiziabher yimesgen

## ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

ቸል ያላለን አምላክ ስንጓዝ ማዕበሉን አቋርጠን

ስለ ማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

አዝማች--------------

የህይወት እስተንፋስ ዘራብን ህያው እንድንሆን

ይህን ላደረገ አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን

ስለማይነገረ ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

አዝማች--------------

ነፋስን ገስፆ ማዕበል አቁሞ የሚያሻግር

የዓለም ፈተና ቢበዛ እሱ መጠጊያችን

ስለ ማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

አዝማች--------------

Dagim endanimot bemotu motin yesharelin

Yeminimekabet tinsaea selamin yeseten

Silemayneger sitotaw egiziabher yimesgen

………azimach………

Kesiol esirat tefeten netsa yewotanibet

Meskelun leseten amlakachin enzemir beiwunet

Silemayneger sitotaw egiziabher yimesgen

………azimach………

ዳግም እንዳንሞት በሞቱ ሞትን የረታልን
የምንመካበት ትንሳኤሰላሙን የሰጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
<u>አዝማች</u>--------------

ከሲኦል እስራት ተፈተን ነፃ የወጣንበት
መስቀሉን ለሰጠን አምላካችን እንዘምር በእውነት
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

<u>አዝማች</u>--------------

## Yeawaj negari kal bebereha ale

Yeigziabherin menged astekaklu eyale
Miskirinetun yohannes kasredan
Libachin begeta melkam menged yihun

Yedenagil memekia yenebiat gedam
Awude ametun barkilin dingil Mariam

Teraraw zik yibel temamawum yikna
Kaltestekakele menged yelemina
Yeigziabherin menged hulachin enmesrit
Marefia endihonen lemechiwum amet

.........azimach.........

## የአዋጅ ነጋሪ ቃል በበረሃ ኤለ

የእግዚአብሔርን መንገድ አስተካክሉ እያለ
ምሥክርነቱን ዮሐንስ ካስረዳን
ልባችን በጌታ መልካም መንገድ ይሁን

የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
አውደ ዓመቱን ባሪርኪልን ድንግል ማርያም

ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና
ካልተስተካከለ መንገድ የለምና
የእግዚአብሔርን መንገድ ሁላችን እንመሥርት
ማረፊያ እንዲሆነን ለመጭውም ዓመት

አዝማች---------------

Kifatina tenkol kelibachin yitfa

Tsidkina rihrahe begna lay yisfafa

Sigwuna demun bekibir agignitenal

Hiwot endihonen getan tematsinenal

………azimach………

Hulet libsoch yalut kemabizat libsun

Lelelew yadilew huletegnawun

Kebedelachin antsan aderah

Bekifu endantefa egna barochih

………azimach………

ክፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ

ጽድቅና ርኅራኄ በእኛ ላይ ይስፋፋ

ሥጋውና ደሙን በክብር አግኝተናል

ሕይወት እንዲሆነን ጌታን ተማጽነናል

አዝማች--------------

ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልበሱን

ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን

ከበደላችን አንጻን አደራህ

በክፉ እንዳንጠፋ እኛ ባሮችህ

አዝማች--------------

## Awude amet lebarko

Barko awude amet (2)

Niai Mariam lemihiret wesahil (2)

## አውደ ዓመት ለባርኮ

ባርኮ ዓውደ ዓመት (2)

ንኢ ማርያም ለምሕረት ወሳሕል (2)

## Yemeskel Mezmur

Werido emeskelu (2)

Emeskelu abriha lekulu (2)

Yomise leiliyaye (2)

Aberih bemeskeliye (2)

Meskel hailine meskel tsiline meskel bezane (2)

Medihanitne leile amene (2)

Tsega nesaine wehiwote erkebine behaile mesekelu leiyesus kristos behaile meskelu (2)

Kiyake egizio neakut wenisebihake egziabiher (2)

## የመስቀል መዝሙር

ወሪዶ እመስቀሉ/2/
እመስቀሉ አብረሐ ለኩሉ/4/

ዮምሰ ለእሊአየ /፪/
አበርህ በመስቀልየ /፬/

መስቀል ኃይልነ መስቀል ጽዕልነ መስቀል ቤዛነ (2)

መድኃኒትነ ለእለ አመነ (2)

ጸጋ ነሳዕነ ወሕይወተ እረከብነ በኃይለ መስቀሉ
ለኢየሱስ ክርስቶስ በኃይለ መስቀሉ (2)

ኪያከ እግዚኦ ነአኩት ወንሴብሐከ እግዚአብሔር (2)

**Hail yeiziabher** new madan yeigziabher tibeb yeigziabher (2)

Animakema begulebetachin

Egziabher new yegna hailachin

**ኃይል የእግዚአብሔር** ነው ማዳን የእግዚአብሔር ጠበብ የእግዚአብሔር (2)

አንመካም በጉልበታችን እግዚአብሔር ነው የእኛ ኃይላችን

## Zemene Tsige

Enze tehakifiyo lehitsanki dingil (2)

Misle Michael (4) fisuh wegebriel

Aklile tsige mariyam legiyorgis ketsela Mengistu

Kibebe gera work (2) aklile tsige

Anti kulo tasegdi lotu (2)

Welekini (2) yisegid wuitu (2)

## ዘመነ ጽጌ

እንዘ ተሐቅፊዮ ለህፃንኪ ድንግል (2)

ምሰለ ሚካኤል (4) ፍሱህ ወገብርኤል 2

አክሊለ ጽጌ ማርያም ቀጸላ መንግሥቱ ለጊዮርጊስ
ከበበ ጌራ ወርቅ (2) አክሊለ ጽጌ

አንቲ ኵሎ ታሰግዲ ሎቱ፣
ወለኪኒ ይሰግድ ውእቱ፡፡

**Tsilat zemuse** etsepatos zesina (2)
Tsenatsil (4) zearon kakin

**Kidane Mihiret** emebet (2)
Neylin (2) kalenibet (2)
Kesemayat belay kalew kemaderiash (2)
Zmare kemolaw kezelalem betish
Yemidir fitretat Mariam Mariam silush (2)
Yekal enat emebeta ney beseregelash (2)
Azmach
Ketsetita wedeb kefikir awudima (2)
Keselamu mender keiwunet ketam (2)
Seali lene kidist wudasesh sisema (2)
Kemichael kegabriel gar neylin kerama (2)
Azmach

**ጽላት ተሙሴ** ዕፀጳጦስ ዘሲና (2)
ጸናጽል (4) ዘአሮን ካህን

**ኪዳነ ምሕረት** እመቤት እመቤት (2)
ነይልን (2) ካለንበት (2)
ከሰማያት በላይ ካለው ከማደርያሽ (2)
ዝማሬ ከሞላው ከዘለዓለም ቤትሽ
የምድር ፍጥረታት ማርያም ማርያም ሲሉሽ (2)
የቃል እናት እመቤቴ ነይ በሰረገላሽ (2)
አዝማች
ከፀጥታ ወደብ ከፍቅር አውድማ
ከሰላሙ መንደር ከእውነት ከተማ (2)
ሰአሊ ለነ ቅድስት ውዳሴሽ ሲሰማ (2)
ከሚካኤል ከገብርኤል ጋር ነይልን ከራማ
አዝማች

Zerfafaw kemisish yiwrede kesemayat (2)
Enbachin yitabes beanchi amalajinet
Yetsion zimara temolach nefsachin (2)
Niai (3) enibel ende abatochachin (2)

Azmach

Fitiretat sidinu beamalajinetish (2)
Yezelalem kidan amanuel setesh
Tiwulid yihin amino bitseit yilishal (2)
Enata memekiaye mirkuza honeshal (2)

Azmach

Yelibin siawayush semitesh zim atiyim (2)
Chigiregnan ayito libish aychekinim
Keayin tikisha fetinesh tidershiletalesh (2)
Kehazen kemekera tasarifiw alesh (2)

Azmach

ዘርፋፋ ቀሚስሽ ይውረድ ከሰማያት (2)
ዕንባችን ይታበስ ባንቺ አማላጅነት
የጽዮን ዘማሪ ተሞላች ነፍሳችን (2)
ንዒ (3) እንበል እንደ አባቶቻችን (2)

አዝማች

ፍጥረታት ሊድኑ በአማላጅነትሽ (2)
የዘላለም ኪዳን አማኑኤል ሰጠሽ
ትውልድ ይህን አምኖ ብፅዕት ይሉሻል (2)
እናቴ መመኪያዬ ምርኩዜ ሆነሻል (2)

አዝማች

የልብን ሲያዋዩሽ ሰምተሽ ዝም አትይም (2)
ችግረኛን አይቶ ልብሽ አይቸከንም
ከዓይን ጥቅሻ ፈጥነሽ ትደርስለታለሽ (2)
ከኃዘን ከመከራ ታሳርፊዋለሽ (2)

**Egziabher birhanena medhanita new** (2)
Yemiyasdenegitegn yemiasferagn man new (2)
Amlakiye memekiyaye new

**Emebeta Mariam eleminish alehu**
Belekiso bewayta fitish wodikialehu
Emebeta simign eleminishalehu (2)
Hazenan chinketan leman enegiralehu
Chigiran gudaten leman awayalehu
Emebeta simign tematsigneshalehu (2)
Hazenu bezabign fetenaw kebedegn
Edemin lichalew ena dekama negn
Yeamanuel enat fetinesh direshilign (2)
Betam tengedagedku liwodik new ena
Eme amalak degifign kumilign kegona
Minim agas yelegn keanchi beker lena (2)

**እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው (2)**
የሚአስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው (2)
አምላኪየ መመኪያየ ነው።

**እመቤቴ ማርያም እለምንሻለሁ**
በለቅሶ በዋይታ ፊትሽ ወድቄያለሁ
እመቤቴ ስሚኝ እለምንሻለሁ/፪/

ኃዘኔን ጭንቀቴን ለማን እነግራለሁ
ችግሬን ጉዳቴን ለማን አዋያለሁ
እመቤቴ ስሚኝ ተማጽኜሻለሁ/፪/

ኃዘኑም በዛብኝ ፈተናው ከበደኝ
እንደምን ልቻለው እኔስ ደካማ ነኝ
የአማኑኤል እናት ፈጥነሽ ድረሺልኝ/፪/

በጥም ተንገዳገድኩ ልወድቅ ነው እኔ
እመ አምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጎኔ
ምንም አጋር የለኝ ካንቺ በቀር ለኔ/፪/

**Giorgis hayal (2) mestegadil**

Gebare teamer (2) kokebe kibir (2)

**Michale slew smun stera**

Yeamlakiye brhan belaye bera

Azagn new beiwunet fitsum azagn (2)

Yemitebikiegn yemiyatsnanagn (2)

Kalekoch gara hizbun yemera

Yemimelales beisat terara

Bahirum sheshe kemaderiawu

Yegeta melak sinawutsew

*Zendowun ashenifual (2)*

*Simun bekibir tsifaul (2)*

ጊዮርጊስ ኃያል(2) መስተጋድል
ኧኸ ገባሬ ተአምር(2) ኮከበ ክብር(2)

**ሚካኤል ስለው ስሙን ስጠራ**

የአምላኬ ብርሃን በላዩ በራ

አዛኝ ነው በእውነት ፍጹም አዛኝ (2)

የሚጠብቀኝ የሚያጽናናኝ (2)

ካለቆች ጋራ ሕዝቡን የመራ

የሚመላለስ በእሳት ተራራ

ባሕሩም ሸሸ ከማደሪያው

የጌታ መልአክ ሲያናውጸው

ዘንዶውን አሸንፏል (2)

ስሙን በክብር ጽፏል (2)

አዝማች

Kebadu gara meda honognal
Yewoyna mezgia tekeftolignal
Alnawotsim ketom alfera
Yegeta melak new kena gara
*Zendowun ashenifual (2)*
*Simun bekibir tsifaul (2)*

Tbitegnawun ashenifotal
Diablos ahun zinarun fetual
Talak tsetita besemay hone
Egziabher bicha simu genene
*Zendowun ashenifual (2)*
*Simun bekibir tsifaul (2)*

ከባዱ ጋራ ሜዳ ሆኖኛል
የወይኔ መዝጊያ ተከፍቶልኛል
አልናወጽም ከቶም አልፈራ
የጌታ መልአክ ነው ከእኔ ጋራ
ዘንዶውን አሸንፏል (2)
ስሙን በክብር ጽፏል (2)
አዝማች

ትዕቢተኛውን አሸንፎታል
ዲያብሎስ አሁን ዝናሩን ፈትቷል
ታላቅ ጸጥታ በሰማይ ሆነ
እግዚአብሔር ብቻ ስሙ ገነነ
ዘንዶውን አሸንፏል (2)
ስሙን በክብር ጽፏል (2)
አዝማች

Michale sikom fetino derashu

Yemikawomun atbikew sheshu

Talaku melak kefit kedeme

Tarik teseta enbachin kome

*Zendowun ashenifual (2)*

*Simun bekibir tsifaul (2)*

ሚካኤል ሲቆም ፈጥኖ ደራሹ

የሚቃወሙን አጥብቀው ሸሹ

ታላቁ መልአክ ከፊት ቀደመ

ታሪክ ተሠራ ዕንባችን ቆመ

ዘንዶውን አሸንፏል (2)

ስሙን በክብር ጽፏል (2)

አዝማች

**Yeyard wub zema dingil emebeta sitotaye nesh (2)**

Bemin andebeta endatis bale kal Mariam lbelishi (2)

Midrina semayu tamrshin yingeru

Fitretat bemulu sile anchi yimeskiru

Tenegiru yemayalk dink new sirashi

Dingil hoy enata amsayam yeleshi

Mariam dingil eredata

Yemitdershilign ney silish bechinketa

Teamirhisnim beayna aychalehu

Tsion silish dingil hoy etegibalehu

**የያሬድ ውብ ዜማ ድንግል እመቤቴ ስጦታዬ ነሽ (2)**

በምን አንደበቴ እምዴትስ ባለ ቃል ማርያም ልበልሽ (2)

ምድርና ሰማዩ ተአምርሽን ይንገሩ

ፍጥረታት በሙሉ ስለ አንቺ ይመስክሩ

ተነግሮ የማያልቅ ድንቅ ነው ሥራሽ

ድንግል ሆይ እናቴ አምሳያም የለሽ

ማርያም ድንግል እረዳቴ

የምትደርሽልኝ ነይ ስልሽ በጭንቀቴ

ተአምርሽንም በዓይኔ አይቻለሁ

ጽዮን ሆይ ስልሽ ድንግል ሆይ እጠግባለሁ

አዝማች

*Yeyard wub zema dingil emebeta sitotaye nesh (2)*

*Bemin andebeta endatis bale kal Mariam lbelishi (2)*

Yeigziabher tibebu beanchi tegeletse

Yeadam zer bemulu kemot amelete

Yemedan miknyat Mariam anchi neshi

Lefitretu hulu meselal yehonshi

Nege balawuk enanim biyasferagn

Anchi kaleshi befitsum alwodkim

Befitsh endikom lemisgana

Mariam libelish betihitian

*የያሬድ ውብ ዜማ ድንግል እመቤቴ ስጦታዬ ነሽ (2)*

*በምን አንደበቴ እምዴትስ ባለ ቃል ማርያም ልበልሽ (2)*

የእግዚብሔር ጥበቡ በአንች ተገለጠ

የአዳም ዘር በሙሉ ከሞት አመለጠ

የመዳን ምክንያት ማርያም አንች ነሽ

ለፍጥረቱ ሁሉ መሰላል የሆንሽ

ነገ ባላውቅ እኔንም ቢያስፈራኝ

አንቺ ካለሽኝ በፍጹም አልወድቅም

በፊትሽ እንድቆም ለምስጋና

ማርያም ልበልሽ በትህትና

*Yeyard wub zema dingil emebeta sitotaye nesh (2)*

*Bemin andebeta endatis bale kal Mariam lbelishi (2)*

Tiwuld bemulu lemisgana yikum

Beanchi silehone yekerelet mergem

Adam keneliju besemay bemidir

Mariam Mariam yibel tamirshin yenager

Chelemaw kefita tegefefe

Mariam bemiljash liba arefe

Kegona ney silish etsnanalehu

Esat gedelun hulunim lafewalehu

Azmach

*የያሬድ ውብ ዜማ ድንግል እመቤቴ ስጦታዬ ነሽ (2)*

*በምን አንደበቴ እምዴትስ ባለ ቃል ማርያም ልበልሽ (2)*

ትውልድ በሙሉ ለምስጋና ይቁም

በአንቺ ስለሆነ የቀረለት መርገም

አዳም ከነልጁ በሰማይ በምድር

ማርያም ማርያም ይበል ታምርሽን ይናገር

ጨለማው ከፊቴ ተገፈፈ

ማርያም በምልጃሽ ለቤ አረፈ

ከጎኔ ነይ ስልሽ እጽናናለሁ

እሳት ገደሉን ሁሉንም አልፈለሁ።

አዝማች

## Yalante lena man lihonegn

Geta hoy fikrh liban retagn
Higih nebere yafa mefcha
Yematikeyer ante bicha

Astemiribet bemerkaba
Kalihin bicha yadmit liba
Kenu bikefam wede mata
Asaw tazeze leante geta

Azmach

## ያለ አንተ ለእኔ ማን ሊሆነኝ

ጌታ ሆይ ፍቅርህ ልቤን ነካኝ
ሕግህ ነበረ ያፌ መፍቻ
የማትቀየር አንተ ብቻ

አስተምርበት በመርከቤ
ቃልህን ብቻ ያድምጥ ልቤ
ቀኑ ቢከፋም ወደ ማታ
አሳው ታዘዘ ለአንተ ጌታ

አዝማች

Wuda libelih shilimata
Betam yeante new sewuneta
Deledelkilign yanena gara
Endalmot argegn endalefera

*Yalante lena man lihonegn*
*Geta hoy fikrh liban retagn*
*Higih nebere yafa mefcha*
*Yematikeyer ante bicha*

Tsetsetegn zara yagnaw werat
Anten salawukih yenorkubet
Fikir neh leka mar wolela
Min hiwot ale keante lela

ውዴ ልበልህ ሽልማቴ
ቤቴም ያንተ ነው ሰውነቴ
ደለደልክልኝ ያነን ጋራ
እንዳልሞት አርገኝ እንዳልፈራ

*ያለ አንተ ለእኔ ማን ሊሆነኝ*
*ጌታ ሆይ ፍቅርህ ልቤን ነካኝ*
*ሕግህ ነበረ ያፌ መፍቻ*
*የማትቀየር አንተ ብቻ*

ጸጸተኝ ዛሬ ያኛው ወራት
አንተን ሳልውቅህ የኖርኩበት
ፍቅር ለካ ማር ወለላ
ምን ሕይወት አለ ከአንተ ሌላ

*Yalante lena man lihonegn*
*Geta hoy fikrh liban retagn*
*Higih nebere yafa mefcha*
*Yematikeyer ante bicha*

*ያለ አንተ ለእኔ ማን ሊሆነኝ*
*ጌታ ሆይ ፍቅርህ ልቤን ነካኝ*
*ሕግህ ነበረ ያፌ መፍቻ*
*የማትቀየር አንተ ብቻ*

Kesafiachinin kesfehewal
Yanen chinkun ken alfenewal
Negem yante new addisu ken
Enzemiralen sitnafiken

ቀሳፊያችንን ቀስፈኸዋል
ያነን ጭንቁን ቀን አልፈነዋል
ነገም ያንተ ነው አዲሱ ቀን
እንዘምራለን ስትናፍቀን

**Enameseginh alen (2) ende abatochachin bemahilet enterahalen**

Endekidusanu lekbrih enzemiralen

Lamlak wudase lefetari kibir

Maleda tenesten misgana sinjemir

Yabatoch zimarra kina mewodisu

Sisema des yilal kebete mekdesu

Azmach

Siriate semay bemidir teserto

Beabatoch libuna yeamlak tibeb molto

Zimaraw feleke ketalaku mekides

Betium zema fetari liwodes

**እንመሰግንህአለን (2) እንደ አባቶቻችን በማኅሌት እንጠራሃለን።**

እንደ ቅዱሳኑ ለክብርህ እንዘምራለን።

ለአምላክ ውዳሴ ለፈጣሪ ክብር

ማላዳ ተነስተን ምስጋና ስንጀምር

ያባቶች ዝማሬ ቅኔ መወድሱ

ሲሰማ ደስ ይላል በቤተ መቅደሱ።

አዝማች

ሥርዓተ ሰማይ በምድር ተሠርቶ

በአባቶች ልቡና የአምላክ ጥበብ ሞልቶ

ዝማሬው ፈለቀ ከታላቁ መቅደስ

በጥዑመ ዜማ ፈጣሪ ሊወደስ

*Enameseginh alen (2) ende abatochachin bemahilet enterahalen*

*Endekidusanu lekbrih enzemiralen*

Dimtsu kesekesegn kekidus teraraw

Yeyared tsenatsil mesenko begenaw

Yetsion denagil lemezmur tenesu

Silus kidus belu simun awodisu

Azmach

Mahiletu sikom seatat mezmuru

Kidusan melaikt abirew sizemru

Fitsum temesetech nefisachin bedesta

Lemisgana sinkom kekidusan terta

Azmach

*እንመሰግንሀአለን(2) እንደ አባቶቻችን በማኅሌት እንጠራሃለን።*

*እንደ ቅዱሳኑ ለክብርህ እንዘምራለን።*

ድምፁ ቀሰቀሰን ከቅዱስ ተራራው

የያሬድ ጸናጽል መሰንቆ በገናው

የጽዮን ደናግል ለመዝሙር ተነሱ

ሥሉስ ቅዱስ በሉ ስሙን አወድሱ

አዝማች

ማኅሌቱ ሲቆም ሰዓታት መዝሙሩ

ቅዱሳን መላእክት አብረው ሲዘምሩ

ፍጹም ተመሰጠች ነፍሳችን በደስታ

ለምስጋና ስትቆም ከቅዱሳን ተርታ

አዝማች

## Zemir zemir alegn liba tenesasa (2)

Yeamlaken cherinet endat biye lirsa
Yaderegelignin endat biye lirsa

Yemikatelew sib befith mindir new
Semayna midir hulu genzebih new
Yalegnin sebsiba banorew kefith
Waga ayhonim geta silecherinetih

Azmach

Yibezal yisefal yeigziabher misgana
Aykomim bezeme maibel newuna
Enkuan dingay kerto garaw binadibign
Yekenferan fira manim aywosdibign

## ዘምር ዘምር አለኝ ልቤ ተነሳሳ (2)

የአምላኬን ቸርነት እንዴት ብየ ልርሳ
ያደረገልኝን እንዴት ብየ ልርሳ

የሚቃጠለው ስብ በፊትህ ምንድር ነው
ሰማይና ምድር ሁሉ ገንዘብህ ነው
ያለኝን ሰብስቤ ባኖረው ከፊትህ
ዋጋ አይሆንም ጌታ ስለ ቸርነትህ

አዝማች

ይበዛል ይሰፋል የእግዚአብሔር ምስጋና
አይቆምም በዘመን ማዕበል ነውና
እንኳን ድንጋይ ቀርቶ ጋራው ቢናድብኝ
የከንፈሬን ፍሬ ማንም አይወስድብኝ

*Zemir zemir alegn liba tenesasa (2)*
*Yeamlaken cherinet endat biye lirsa*
*Yaderegelignin endat biye lirsa*

Yepawlos yesilas mekera bitsena
Altewum kinawun yeamlaken misgana
Liastilegn aychilm esir senseleta
Alebign wuleta lesemayu abate
Azmach
Yetederegelet bizu yetekebele
Yinoral befikru eyetekatele
Kibran hulu tiche lizemirilih
Yih new chilotaye lante misetih

***ዘምር ዘምር አለኝ ልቤ ተነሳሳ (2)***
*የአምላኬን ቸርነት እንዴት ብየ ልርሳ*
*ያደረገልኝን እንዴት ብየ ልርሳ*

የጳውሎስ የሲላስ መከራ ቢጸና
አልተውም ቅኔውን የአምላክን ምስጋና
ሊያስጥለኝ አይችልም እስር ሰንሰለቴ
አለብኝ ውለታ ለሰማዩ አባቴ

አዝማች
የተደረገለት ብዙ የተቀበለ
ይኖራል በፍቅሩ እየተቃጠለ
ክብሬን ሁሉ ትቸ ልዘምርልህ
ይህ ነው ችሎታዬ ላንተ ምስጥህ